የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ኅዳር ፳፩ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 4
ADDIS ABABA - 30th November, 2000

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፪/፲፱፻፺፫ ዓ·ም
ከግሪክ መንግሥት ጋር የተደረገው የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............. ገጽ ፩ሺ፬፻፴፩

CONTENTS

Proclamation No. 222/2000
The Economic and Technical Cooperation Agreement with the Government of the Hellenic Republic Ratification Proclamation ........................ Page 1431

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፪/፲፱፻፺፫
### ከግሪክ መንግሥት ጋር የተፈረመውን የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በግሪክ መንግሥት መካከል የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ለማድረግ እ·ኤ·አ· ኖቬምበር ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ አቴንስ ላይ ስምምነት የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው ተዋዋዮቹ ሀገሮች በየሕገመ ንግሥታዊ ሥርዓቶቻቸው መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን አንዱ ለሌላው ካሳወቀበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር ፴ ቀን በኋላ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተገለጸ በመሆኑ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከግሪክ መንግሥት ጋር የተደረገው የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፪/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 222/2000
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON ECONOMIC AND TECHNICAL COOPERATION WITH THE GOVERNMENT OF THE HELLENIC REPUBLIC

WHEREAS, an Agreement on economic and technical cooperation, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Greece, was signed in Athens on the 20th day of November, 1998;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force thirty (30) days after the date on which the contracting parties notify each other of the completion of the constitutional procedures required for this purpose in each country;

WHEREAS, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 30th day of November, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This proclamation may be cited as the "Economic and Technical Cooperation Agreement with the Government of the Hellenic Republic Ratification Proclamation No. 222/2000"

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በግሪክ መንግሥት መካከል የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ለማድረግ እ·ኤ·አ· ኖቬምበር ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ አቴንስ ላይ የተፈረመው ስምምነት ጸድቋል።

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከህዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on Economic and Technical Cooperation signed in Athens on the 20th day of November, 1998 between the Government of the Hellenic Republic and the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is Ratified.

3. *Effective Date*

This proclamation shall enter into force as of the 30th day of November, 2000.

Done at Addis Ababa, this 30th day of November, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE